የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፖ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: የካቲት 29 2015

ቁጥር/REF NO: ፩/286/384/15

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
ለሐረማያ ዩኒቨርስቲ
ለሀዋሳ ዩኒቨርስቲ
ለመደወላቡ ዩኒቨርስቲ
ለሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ
ለአርባምንጭ ዩኒቨርስቲ
ለሰመራ ዩኒቨርስቲ
ለአክሱም ዩኒቨርስቲ
ለመቐለ ዩኒቨርስቲ
ለወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ
ለዲላ ዩኒቨርስቲ
ለደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ
ለአምቦ ዩኒቨርስቲ
ለቡሌሆራ ዩኒቨርስቲ
ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ
ለሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ
ለወለጋ ዩኒቨርስቲ
ለወሎ ዩኒቨርስቲ
ለደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ
ለአሶሳ ዩኒቨርስቲ
ለወልቂጤ ዩኒቨርስቲ
ለደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ
ለድሬዳዋ ዩኒቨርስቲ
ለባህርዳር ዩኒቨርስቲ
ለጎንደር ዩኒቨርስቲ
ለጅማ ዩኒቨርስቲ
ለጅግጅጋ ዩኒቨርስቲ
ለዋቸሞ ዩኒቨርስቲ
ለአዲግራት ዩኒቨርስቲ
ለመቱ ዩኒቨርስቲ
ለጋምቤላ ዩኒቨርስቲ
ለወልዲያ ዩኒቨርስቲ
ለደባርቅ ዩኒቨርስቲ
ለመቅደላ አምባ ዩኒቨርስቲ
ለእንጅባራ ዩኒቨርስቲ
ለደምቢዶሎ ዩኒቨርስቲ
ለወራቤ ዩኒቨርስቲ
ለቦንጋ ዩኒቨርስቲ
ለጂንካ ዩኒቨርስቲ
ለቀብሪደሃር ዩኒቨርስቲ
ለአዳቡልቱም ዩኒቨርስቲ
ለሰላሌ ዩኒቨርስቲ
ለአዲስ አበባ ሳይ/ቴክ/ ዩኒቨርስቲ
ለአዳማ ሳይንስና ቴክ/ ዩኒቨርስቲ
ለኮተቤ የትምህርትዩኒቨርሲቲ
ለራያ ዩኒቨርስቲ
ለቦረና ዩኒቨርስቲ

ባሉበት

**ጉዳዩ፡- በአዲሱ መዋቅር መሠረት የአመራር ቦታዎች ምደባ የአፈጻጸም አቅጣጫን ይመለከታል፡፡**

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መዋቅራዊ አደረጃጀትና የሰው ኃይል ጥናት ከዩኒቨርስቲዎች በተወጣጡ ባለሙያዎችና የሥራ ኃላፊዎች፣ ከትምህርት ሚኒቴርና ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በጋራ በመሆን ሲከናወን መቆየቱ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም አሁን ላይ መዋቅራዊ አደረጃጀቱና የሰው ኃይል ጥናቱ በመጠናቀቅና ለትግበራ ወደ ተቋሞቻችሁ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በኩል ጸድቆ እየተላከ ስለሆነ በሁሉም ተቋማት ወጥ የሆነ አፈፃጸም ለማስፈን ያመች ዘንድ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተዘጋጀውን------ገጽ የአፈፃጸም አቅጣጫ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን አሳውቃለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ
ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት (ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ)
ለአስተዳደርና መሰረተ ልማት ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ለተቋማት አደረጃጀትና አመራር ዴስክ
ትምህርት ሚኒስቴር

CamScanner

# በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት
# በአዲሱ መዋቅር መሰረት የሰው ኃይል ምደባ
# የአፈጻጸም አቅጣጫ

የካቲት/ 2015 ዓ.ም

ትምህርት ሚኒስቴር

CamScanner

# መግቢያ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ተደራሽነት፣ፍትሀዊነት፣አግባብነትና ጥራት የሴክተሩ የርብርብ ማዕከል ሆኖ እየተሰራበት ይገኛል። በመሆኑም በዘርፉ የሚከናወኑ የመማር ማስተማር፣ ጥናትና ምርምር እና የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች የሀገሪቱን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ሊፈቱ በሚችሉበት አግባብ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል። ሆኖም ግን የትምህርት ጥራት መጓደል ቁልፍ ችግር ሆኖ ተገኝቷል። ሥለሆነም በቀጣይ የስትራቴጅክ ዘመን የትምህርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ጉዳዮችን በሴክተር ደረጃ የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎችን በማከናወን በቁርጠኝነት ልንሰራበት የሚገባ ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡፡

በዚህ አግባብ ከሪፎርም ሥራዎች ውስጥ አንዱ የተቋማትን አደረጃጀት እና መዋቅር ወጪ ቆጣቢ፣ተመጋጋቢና ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ በማስቻል የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ መደላድል መፍጠር አስፈላጊ ነው። ይህን ታሳቢ በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊ አደረጃጀትና መዋቅር በማዕከል ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን አሳታፊና ባለቤት በሆኑበት አግባብ መዋቅሩ ለአፈፃጸም ዝግጁ መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ይህንን አደረጃጀትና መዋቅር ተግባራዊ ለማድረግ ለሰው ኃይል ምደባው ይህ የአፈፃጸም አቅጣጫ ተዘጋጅቷል፡

Federal Democratic Republic Ethiopia
Ministry of Education



CamScanner

## ክፍል አንድ

### አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 1፡- አጭር ርዕስ**

ይህ ሰነድ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰው ኃይል አመዳደብ የአፈፃጸም አቅጣጫ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፤

በዚህ ማዕቀፍ ጥቅም ላይ የዋሉ ቁልፍ ቃላት ፍች እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1. መዋቅር ማለት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ተቋማዊ አደረጃጀት ተግባራዊ ለማድረግ በ2015 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረገውን መዋቅር ማለት ነው፡፡
2. ከፍተኛ ትምህርት ማለት በሥነ ጥበብ በማህበራዊ ሳይንስ እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃና ድህረ ምረቃ የድግሪ ፕሮግራሞች ትምህርት የሚሰጥ ማለት ነው፡፡
3. የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማለት ለትምህርት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነና በጀቱ በፌደራል መንግስት የሚሸፈን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማለት ነው፤
4. ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፡፡
5. ዳይሬክተር' ማለት በአካዳሚክ ዘርፍ ትምህርታዊ ፕሮግራሞች እና የምርምር ስራዎችን የሚመራ አመራር ማለት ነው፡፡
6. ሥራ አስፈፃሚ ማለት በአስተዳደር ዘርፉ አንድ የሥራ ክፍል የሚመራ አመራር ማለት ነው፣
7. ዲን ማለት በከፍተኛ ትምህርት ኮሌጂ፣ በትምህርት ክፍልና በተማሪዎች አገልግሎት ክፍል ስራን የሚመራ አመራር ነው፡፡

**አንቀጽ 2፡- በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡**

**አንቀጽ 3፡- የአፈፃጸም አቅጣጫው አስፈላጊነት**



CamScanner

በ2015 ዓ.ም ተግባራዊ በመደረግ ላይ የሚገኘውን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማዊ መዋቅር ፍትሀዊ በሆነ የውድድር ሥርዓት ተዘጋጅተው በጸደቁ መደቦች ላይ ምደባ እንዲካሄድ ለማስቻል ነው፡፡

**አንቀጽ 4፡- ዓላማ**

ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተዘጋጀውን መዋቅራዊ ጥናት ፍትሀዊ በሆነ መንገድ የሰው ኃይል ምደባ በማስፈጸም ቀልጣፋና ውጤታማ የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ለማስፈን እንዲሁም የዩኒቨርሲቲዎችን ተልዕኮና የትኩረት መስካቸውን ለማሳካት የሚያስችል ብቃት ያለው የሰው ኃይል እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ 5፡- የሰው ኃይል ማሟያ ስልቶች**

1. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተመዝነው ደረጃ የወጣላቸውን የሥራ መደቦች ውድድርን መሰረት ባደረገ መልኩ የሰው ኃይል ማሟላት፣
2. የዘላቂነት ባህሪ በሌላቸው የሥራ መደቦች ላይ በሁኔታዎች አስገዳጅነት ጊዜያዊ ሰራተኞችን መቅጠር፤
3. ሥራዎችን በፕሮጀክት አደረጃጀት መሰረት ማሰራት ሲያስፈልግ ልዩ ሙያዊ ችሎታና ብቃት ያላቸውን ሰራተኞች በጊዜያዊነት ቀጥሮ ማሰራት፣

**አንቀጽ 6፡- በድልድል ወቅት በአካዳሚክ ዘርፉ የኃላፊነት ቦታዎች ለምደባው ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች፤-**

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተዘጋጀውን አዲሱን መዋቅራዊ አደረጃጀት ተግባራዊ ለማድረግ ከአመራሩ እስከ.ባለሙያ ድረስ ያለውን የሰው ሀይል ለማሟላት ታሳቢ መደረግ ያለባቸው ጉዳዮችን በተመለከተ፡-

ሀ. እስከ 15,000 መደበኛ ተማሪዎች ያሉት ተቋም አንድ የተማሪዎች አገልግሎት ዲን እና የተማሪዎች ስብዕና ግንባታ ምክትል ዲን ይኖሩታል፣

ለ. ከ15,000 በላይ መደበኛ ተማሪዎች ያሉት ተቋም አንድ የተማሪዎች አገልግሎት ዲን፣ አንድ የተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ዲን እና አንድ የተማሪዎች ስብዕና ግንባታ ምክትል ዲን ይኖሩታል፣

## አንቀጽ 7፦ ኮሌጅ ዲንና ትምህርት ክፍል ኃላፊ

በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመዋቅሩ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ የኮሌጅ ምክትል ዲንን በሚመለከት በሚያስተዳድረው የሰው ኃይልና ባለው የትምህርት ክፍል ብዛት በሚከተለው አግባብ ይወሰናል፤

1. እስከ 100 መምህራን፣ እስከ 1500 የመደበኛ ተማሪዎች እና እስከ አምስት የትምህርት ክፍሎች ያለው ኮሌጅ በኮሌጅ ዲን ብቻ የሚመራ ይሆናል።
2. ከ100 በላይ መምህራን፣ ከ1500 በላይ የመደበኛ ተማሪዎች እና ከአምስት የትምህርት ክፍሎች በላይ ያለው ኮሌጅ ምክትል ዲን ይኖረዋል።
3. እስከ 50 መምህራን እና እስከ 1000 መደበኛ ተማሪዎች ያለው ትምህርት ክፍል በትምህርት ክፍል ኃላፊ ብቻ የሚመራ ይሆናል።
4. ከ50 በላይ መምህራን እና ከ1000 በላይ መደበኛ ተማሪዎች ያለው ትምህርት ክፍል ምክትል ትምህርት ክፍል ኃላፊ ይኖረዋል።

## አንቀጽ 8፦ በአካዳሚክና በምርምር ዘርፍ

ሀ. በአካዳሚክና በምርምር ዘርፍ የተደራጁ ዳይሬክቶሬቶች ተቋማቱ ባላቸው ፕሮግራሞች ብዛት፣ የምርምር ማዕከላት ብዛት፣ የካፓስ ቁጥርና ከዋናው ግቢ ያላቸው ርቀት ግምት ውስጥ በማስገባት የአካዳሚክ የምርምር ኦፊሰሮች ይኖረዋል።

ለ. በአካዳሚክ ዘርፉ የሚኖሩ ኃለፊነቶች በተመለከተ፤ ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የአካዳሚክ ዳይሬክቶሬቶች፣ ኮሌጂ ዲን፣ ምክትል ኮሌጂ ዲን፣ ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና ምክትል ትምህርት ክፍል ኃላፊ የኃላፊነት ቦታዎች ናቸው።



CamScanner

## ክፍል ሁለት

### አንቀጽ 9፦ የአመራር ምደባ

በአዲሱ መዋቅር የተካተቱ የአመራር መደቦች የሰው ኃይል ምደባ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የከፍተኛ አመራሮችና አሰያየም መመሪያ ቁጥር 002/2011 መሰረት ይከናወናል።

### አንቀጽ 9.1 የምክትል ፕሬዚዳንቶች ብዛትን በተመለከተ፤-

1. የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የምርምርና ትብብር ምክትል ፕሬዚዳንት እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ይኖራቸዋል።
2. የአፕላይድ ሳይንስ ዩኒቨርሲቲዎች የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ይኖራቸዋል።
3. የአጠቃላይ ዩኒቨርሲቲዎች የአካዳሚክ፣ የምርምር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይኖራቸዋል።
4. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሰቲዎች የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት፣ የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምክትል ፕሬዚዳንት እና የአስተዳደርና ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ይኖራቸዋል።

### አንቀጽ 10፦ ፕሬዚዳንትና የምክትል ፕሬዚዳንቶች ሽግሽግ በተመለከተ የሥራ አመራር ቦርዱ የሚከተሏቸው አቅጣጫዎች፦

1. የፕሬዚዳንት ምደባ በሚመለከት የአገልግሎት ጊዜያቸውን እስከሚያጠናቅቁ ባሉበት ይቀጥላሉ።
2. ምክትል ፕሬዚዳንቶችን በተመለከተ ቀደም ብሎ ተፈቅዶ ሲሰራበት የነበረው የኃላፊነት ቦታ አሁን በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አዲስ ጸድቶ ከመጣው የኃላፊነት ቦታ ጋር እኩል ከሆነ በአዲሱ የኃላፊነት ቦታ ስያሜ መሰረት የስያሜ ማስተካከያ ተደርጎ አሁን በኃላፊነት ያሉት አመራሮች የኃላፊነት ጊዜያቸውን እስኪያጠናቅቁ ድረስ በያዙት የኃላፊነት ቦታ እንዲቀጥሉ ይደረጋል።

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

3. ምክትል ፕሬዚዳንቶችን በተመለከተ ቀደም ብሎ ተፈቅዶ ሲሰራበት የነበረው የኃላፊነት ቦታ አሁን በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን አዲስ ጸድቆ ከመጣው የኃላፊነት ቦታ ቀንሶ ከመጣ በአዲሱ የኃላፊነት ቦታ ስያሜ መሰረት የስያሜ ማስተካከያ ተደርጎ ማወዳደርና ማሸጋሸግ በማድረግ እስካሁን በኃላፊነት የቆዩበት ጊዜ ታሳቢ ተደርጎ ቀሪ የኃላፊነት ጊዚያቸውን እስከሚያጠናቅቁ ድረስ ብቻ በኃላፊነት እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡
4. ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገልግሎት ጊዚያቸውን ለመጨረስ ሦስት ወራት እና በታች የቀራቸው ምክትል ፕሬዚዳንቶች ለሁለተኛ ጊዜ ብቻ ከሌሎች አመልካቾች ጋር ተወዳድረው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአመራሮች አሰያየም መመሪያ ቁጥር 002/2011 መሰረት እንዲመደቡ ይደረጋል፡፡
5. ሌሎች የኃላፊነት መደቦችን በተመለከተ ከላይ በተራ ቁጥር 3 የተጠቀሰውን የምክትል ፕሬዚዳንቶችን የሽግሽግ መርህን መሰረት በማድረግ የዩኒቨርሲቲው ቦርድ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ11፡- ሌሎች የአካዳሚክ ኃላፊነቶችን በተመለከተ፡-**

1. የምክትል ፕሬዚዳንቶች ልዩ ረዳትን በተመለከተ የአካዳሚክ ሰራተኛ የሆነ/የሆነች ውድድርን መሰረት በማድረግ የሚመደብ ይሆናል፡፡
2. የኮሌጂ ዲን፣ ምክትል ዲኖችን፣ በተመለከተ የአገልግሎት ጊዜያቸው እስከሚጠናቀቅ ድረስ ተገምግመው ጥሩ አፈጻጸም ያላቸው በያዙት የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡
3. የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችና ምክትል ትምህርት ክፍል ኃላፊዎችን በተመለከተ የአገልግሎት ጊዚያቸውን እስከሚጨርሱ ድረስ ተገምግመው ጥሩ አፈጻጸም ያላቸው በያዙት እንደሚቀጥሉ ታሳቢ ተደርጎ ጊዜአቸውን ያጠናቀቁ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች እና ምክትል የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች በሌሎች ተወዳዳሪዎች የሚተኩ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 12፡-የአስተዳደር ዘርፍ አመራሮችን በተመለከተ፡-**

በአስተዳደር ዘርፍ ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች ምደባ በተመለከተ ሰቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣቸው መመሪያዎችና ሰርኩላሮች መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 13፡- ካምፓስ ያላቸው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተመለከተ**

ከዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ የራቀ ካምፓስ እና የተማሪ ቁጥር ከ 1000 በላይ ከሆነ ካምፓሱን በካምፓስ ኤክስኪዩቲቭ ዳይሬክተር የሚተዳደር ሆኖ ምደባዉም ከአካዳሚክ ሰራተኛ በውድድር የሚመደብ ይሆናል፤ አፈፃጸሙ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የከፍተኛ አመራር አሰያየም መመሪያ ቁጥር 002/2011 መሰረት ይሆናል።

Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education